

# የኢየሱስ ማንነት በጴጥሮስ አንደበት

- ኢየሱስ ክርስቶስ  ፊሊጶስ ቂሳሪያ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ ማስተማር ጀምሮአል። እንደልማዱም ለመፀለይ ብቻውን ወደአንድ ስፍራ ሄደ። ደቀመዛሙርቱም አገኙት። እርሱም ይህን ጥያቄ ጠየቃቸው፣ “ለመሆኑ ሰዎች እኔን ማን ይሉኛል?”

- ሰዎች ስለኢየሱስ ክርስቶስ ማንነት ብዙ የሚሏቸው ነገሮች ነበሩ። አንዳንዶች እርሱ መጥምቁ ዮሐንስ ወይንም ኤልያስ ከሙታን ተነስቶ ኢየሱስ በሚል ስም ተገልጦ እንደመጣ ያምናሉ። ሌሎች ደግሞ ኤርምያስ ወይንም ከቀድሞ ነቢያት አንዱ ወደምድር ተመልሶ እንደመጣ ያምናሉ።

- ኢየሱስም ደቀመዛሙርቱ ስለእርሱ ማንነት የሚሉትን መስማት ፈለገ። በዚህን ጊዜ ስምኦን ጴጥሮስ እንዲህ አለ፣ “አንተ ክርስቶስ የህያው የእግዚአብሔር ልጅ ነህ።”  ለመሆኑ ጴጥሮስ እንዲህ እርግጠኛ ሊሆን የቻለው እንዴት ነው?

- ለዚህ መልሱን የሚሰጠን ኢየሱስ ነው።  ስምኦንን፣ “የዮና ልጅ ስምኦን ሆይ።” ብሎ ከጠራው በኋላ ጴጥሮስ የኢየሱስን ትክክለኛ ማንነት የተረዳው በመለኮታዊ መገለጥ እንደሆነ ነገረው። እግዚአብሔር እራሱ ይህን ምስጢር ለጴጥሮስ እንደገለጠለት ኢየሱስ ተናገረ።

- ኢየሱስ በመቀጠልም ቤተክርስቲያኑን እንደሚመሠርትና ምንም አይነት ሰይጣናዊ ኃይል ሊቋቋማት ወይንም ሊያሸንፋት እንደማይችል ተናገረ። የእርሱ የሆኑት ክፉን እንደሚያሸንፉና ባለድሎች እንደሚሆኑ ኢየሱስ አረጋገጠ።

ጴጥሮስም የመንግስተ ሰማይ “ቁልፍ” ይኖረዋል። ማለትም ለሰዎች እግዚአብሔርን ስለሚያስደስቱትና ስለማያስደስቱት ነገሮች ይነግራቸዋል ማለት ነው። ጴጥሮስ የእግዚአብሔር አፍ ሆኖ ሰዎችን ያስተምራል። ሰዎችም ጴጥሮስ ያስተማራቸውን ነገር ይታዘዛሉ። ኢየሱስም ጴጥሮስን እንዲህ አለው፣ “በምድር ያሰርከው ሁሉ በሰማይ የታሰረ ይሆናል፤ በምድር የፈታኸው ሁሉ ደግሞ በሰማይ የተፈታ ይሆናል።”

❋ ከዚያም ኢየሱስ ለጥቂት ጊዜ የእርሱን ማንነት ለሰዎች እንዳይናገሩና በምስጢር እንዲይዙት ለደቀመዛሙርቱ ነገራቸው።

❋ ጴጥሮስ የኢየሱስን መሞት በፍፁም ማየትም ሆነ ማሰብ አይፈልግም ነበርና እንዲህ አለ፣ “ይህ በፍፁም አይሆንም፤ አንተ መሞት የለብህም!” ኢየሱስ ግን ይህን የተናገረው ጴጥሮስ ራሱ ሳይሆን ሰይጣን እንደሆነ ስላወቀ፣ “አንተ ሰይጣን ከእኔ ራቅ!” አለው።

❋ ከሳምንት በኋላም ኢየሱስ ጴጥሮስን፣ ያዕቆብንና ዮሐንስን ይዞ ወደአንድ ተራራ ወጣ። አይናቸው እያየም ተለወጠ። ልክ እንደ ብሩህ ፀሐይ አንፀባረቀ። ይህም ለነጴጥሮስ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ ተጨማሪ ማረጋገጫ ነበር።

*ይህ ታሪክ የሚገኘው በማቴዎስ ወንጌል በምዕራፍ 16፡ 13 – 29 ውስጥ ነው።*